# ካፒታልን ለማሳደግ የዋለ የአክስዮን የትርፍ ድርሻ ከገቢ ግብር ነፃ እንዲሆን የተወሰኑ የሥራ መስኮችን ለማስታወቅ የወጣ መመሪያ

ባለሀብቶች የሚያገኙትን የአክስዮን ትርፍ ድርሻ መንግሥት ትኩረት በሰጣቸው የሥራ መስኮች መልሰው በሥራ ላይ በሚያውሉበት ጊዜ ከግብር ነፃ እንዲሆኑ መፍቀዱ ኢንቨስትመንትን በማበረታታት ረገድ አጋዥነት እንዳለው በመታመኑ፤

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሚያዝያ 29 ቀን 1996 በቁጥር አመ3/16/28/100 በተፃፈ ደብዳቤ የገቢዎች ሚኒስቴር በየጊዜው በሚያወጣው ዝርዝር በሚመለከቱ የኢንቨስትመንት መስኮች፣ ባለሀብቶች ያገኙትን የአክስዮን ትርፍ ድርሻ የኩባንያውን ካፒታል ለማሳደግ ካዋሉ ከገቢ ግብር ነፃ እንዲሆኑ የወሰነ በመሆኑ፤

የገቢዎች ሚኒስቴር በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 26 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል::

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «ካፒታልን ለማሳደግ የዋለ የአክስዮን ትርፍ ድርሻን ከገቢ ግብር ነፃ እንዲሆን ለማድረግ የተፈቀዱ የሥራ መስኮችን ለማስታወቅ የወጣ የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 17/1996» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## 2. ትርጓሜ

1. «ባለሥልጣን» ማለት የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ነው::
2. «ኩባንያ» ማለት የአክስዮን ማህበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ነው::
3. «የአክስዮን ትርፍ ድርሻ» ማለት የአክስዮን ባለቤት የሆኑ ሰዎች ኩባንያው ከሚያገኘው ትርፍ በአክስዮናቸው መጠን የሚያገኙት ገቢ ነው::
4. «አዋጅ» ማለት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 ነው::

## 3. ከግብር ነፃ የሆኑ የሥራ መስኮችን ስለማስታወቅ

ከዚህ በታች በተመለከቱ የሥራ መስኮች ከተሠማሩ ኩባንያዎች በስተቀር ባሉ የሥራ መስኮች የተሠማሩ ኩባንያዎች የአክስዮን ባለሀብቶች ያገኙትን የትርፍ ድርሻ የኩባንያውን ካፒታል ለማሳደግ ካዋሉ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 34 መሠረት ሊከፈል ከሚገባው ግብር ነፃ ይሆናሉ ፡

Records and Documentation Section

ሀ. ባለኮከብ ደረጃዎችን የማይጨምሩ ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ፔንሲዮኖች፣ ሻይ ቤቶች፣ ቡና ቤቶች፣ መጠጥ ቤቶች፣ የምሽት ክበቦች፣ ዐለም አቀፍ ደረጃ የሌላቸው ሪስቶራንቶችና ምግብ ቤቶች፣

ለ. የንግድ ሥራዎች ማለትም የጅምላ፣ የችርቻሮ እና አስመጪነት ሥራ፣

ሐ. የጥገና አገልግሎት ሥራ፤

መ. የንግድ መንገድ ትራስፖርትና የመኪና ማከራየት አገልግሎት ሥራ፣

ሠ. የፖስታና ኩሪየር አገልግሎት ሥራ፣

ረ. ለንግድና ለመኖሪያ የሚሆኑ ቤቶችና ሕንፃዎችን ሠርቶ ማከራየትና መሸጥ፣

ሰ. የአማካሪነት ሥራ፣

ሸ. የማስታወቂያ ሥራ፣

ቀ. የፊልምና መሰል ሥራዎች፣

በ. የሬዲዮና ቴሌቪዥን ሥርጭት አገልግሎት ሥራ፣

ተ. የሲኒማና ቲያትር ቤቶች አገልግሎት ንግድ ሥራ፣

ቸ. የጉምሩክ አስተላላፊነት ንግድ ሥራ፣

ኀ. የላውንደሪ አገልግሎት ንግድ ሥራ፣

ነ. የጉዞ ወኪልነት፣ የንግድ ረዳትና የትኬት መሸጫ አገልግሎት ንግድ ሥራ

ኘ. የሎተሪና የመሳሰሉ ሥራዎች፤

## 4. የኩባንያው ኃላፊነት

በአዋጁ አንቀጽ 34 በተደነገገው መሠረት ኩባንያው ለባለአክሲዮኖች የሚያከፋፍለውን የአክስዮን ትርፍ ድርሻ በአዋጁ አንቀጽ 54(3) በተወሰነው ጊዜ ውስጥ:-

1. ለእያንዳንዱ ባለአክስዮን የሚደርሰውን የአክስዮን ትርፍ ድርሻ መጠን፣
2. ባለአክስዮኖች የአክስዮን ትርፍ ድርሻቸውን የኩባንያውን ካፒታል ለማሳደግ እንዲውል የወሰኑ መሆናቸውን የሚገልጽ ሰነድ፤

3. የአክስዮን ትርፍ ድርሻው የኩባንያውን ካፒታል ለማሳደግ በመዋሉ ምክንያት የኩባንያው ካፒታል በምን ያህል መጠን እንዳደገ የሚያብራራ መግለጫ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል::

## 5. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስትር ተፈርሞ ከወጣበት ዕለት አንስቶ ተፈፃሚነት ይኖረዋል::

ጌታቸው በላይ
የገቢዎች ሚኒስትር

በገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ክፍል
Ministery of Revenues
Records and Documentation Section